# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፣የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 13 ነሐሴ 8 2000 ዓ.ም

## "ረሀቡ እየከፋ ስለሆነ አስቸኳይና ተጨማሪ ዕርዳታ ያስፈልገናል" ዶክተር አበራ ዴሬሳ እና አቶ ስምዖን መቻሌ

## "ረሀብ የለም" መለስ ዜናዊ(ለሎሳንጀለስ ታይምስ)

## "መንግስት በዜጎች ላይ ወንጀል ፈፅሟል"ተቃዋሚዎች

ሪፖርታዥ

በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሀብ እየከፋና አድማሱን እያሰፋ በመምጣቱ ቀደም ሲል ከተጠየቀው በላይ፤ ተጨማሪና አስቸኳይ ዕርዳታ ያስፈልጋል ሲሉ የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር እና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዓለማቀፉን ማህበረሰብ ተማፀኑ።

የገጠር ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር አበራ ደሬሳ እና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዳይሬክተር አቶ ስምዖን መቻሌ የድረሱልን ጥሪውን ያቀረቡት፤ መለስ ዜናዊ ፦"በኢትዮጵያ ረሀብ የለም"በማለት ለሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ ፤ቃለ-ምልልስ በሰጠበት ተመሣሳይ ወቅት ነው።

ዶክተር አበራና አቶ ስምዖን በጋራ ለውጪ አገር ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ በየጊዜው የረሀብተኞች ቁጥር እያሻቀበ መምጣቱን በማመን፤ አሁን በአገሪቱ መጋዘኖች ለተረጅዎች ካለው 20 ሽህ ሜትሪክ ቶን እህል፤ በትንሹ 15 ጊዜ እጥፍ የሚሆን ተጨማሪ የዕርዳታ እህል በአስቸኳይ ስለሚያስፈልግ ለጋሽ አገራት የእርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉ ተማፅነዋል።

ተማፅኖ እንዳቀረቡት ባለስልጣናት ገለፃ ከሆነ፤ በአስቸኳይ የሚፈለገው የእርዳታ እህል መጠን ወደ 300 ሽህ ሜትሪክ ቶን የሚጠጋ ሲሆን፤ይህም የዕርዳታ መጠን ከጥቂት ወራት የሚያልፍ አይደለም።

ሁኔታውን ተዘዋውረው የጎበኙ የግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ተወካዮችና የዓለማቀፍ ዜና ዘጋቢዎች፤ ረሀቡና ችጋሩ የዛሬ ሦስትና አራት ወር ከነበረበት በእጅጉ እንደከፋና የተረጅዎችም አሀዝ ከያኔው በእጥፍ ሊጨምር እንደሚችል በመግለፅ ላይ ይገኛሉ።በተለይ በደቡብ ክልል ረሀቡ እያደረሰ ያለው ጉዳት እጅግ ዘግናኝ ደረጃ ላይ መድረሱን የገለፁት ዓለማቀፍ ሚዲያዎች፤ከዚሁ ክልል ብቻ በየቀኑ በአማካይ እስከ 400 የሚደርሱ ህፃናት በምግብ እጦት እየሞቱ እንደሆነ አጋልጠዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በዚሁ ተመሣሳይ ወቅት በጉዳዩ ዙሪያ ከሎስአንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ ጋር ቃለ-ምልልስ ያደረገው መለስ ዜናዊ፦"በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ረሀብ የለም" በማለት የአደባባይ ድብብቆሽ ለመጫዎት ሞክሯል።" በአሁኑ ወቅት በእኛ ዕይታ ረሀብ የለም፤ አስቸኳይ ዕርዳታ ግን እንፈልጋለን" በማለት እርስበርሱ የሚጣረስ ነገር የተናገረው መለስ፤ "በኢትዮጵያ ይሄ እንደማይከሰት አድርጎ ማሰብ ደደብነት ነው" በማለት በዓለማቀፉ ማህበረሰብ ላይ የስድብ አፉን አላቋል።

ሆኖም፤ የዕርዳታ ተማፅኖውን በባለስልጣኖቹ አፍ እያሰማ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" በሚል ፈሊጥ ወደ ዝልፊያ መንደርደሩ፤ ለብዙዎች ትርጉም የለሽ ባዶ የዕብደት ጩኸት ከመሆን አልፎ፤ አንዳችም ስሜት አልሰጠም።የተጨማሪ አሰቸኳይ ዕርዳታ ተማፅኖ መቅረቡን በተመለከተ አገር ቤት የሚንቀሣቀሱ ተቃዋሚዎች በሰጡት አስተያየት የመለስን አገዛዝ በወንጀለኛነት ከሰዋል።"መንግስት ረሀቡን በመደበቅ ፤ዓለማቀፉ ህብረተሰብ በወቅቱ ረሀብተኛውን እንዳይረዳ አድርጓል። አሁን ሰው መሞት ጀምሯል።ስለዚህም መንግስት በዜጎች ላይ ወንጀል ፈፅሟል" ብለዋል-ተቃዋሚዎቹ።"መንግስት ወትሮም የረሀብተኞች ቁጥር ጠፍቶት ሳይሆን፤ 'በየጊዜው ዕድገት አስመዘገብኩ እያልኩኝ ብዙ ሚሊዮን ህዝብ ተራበብኝ ብል መሣቂያ መሣለቂያ እሆናለሁ' በሚል ስጋት ነው ጉዳዩን ይፋ ለማውጣት ያልደፈረው" ያሉት ተቃዋሚዎች፤ " ጉዳዩን ከፖለቲካ ጋር ስላያያዘውም፤ የዜጎችን ህይወት በመታደግ ፋንታ የረሀብተኞችን ቁጥር በመደመርና በመቀነስ ሥራ ላይ ተጠምዶ ከርሟል" ብለዋል።ስለዚህም፤ በደሀው ህዝብ ላይ ታሪክ ይቅር ሊለው የማይችል ዘግናኝና ከባድ ወንጀል መፈፀሙን አስምረውበታል። ወደገጽ 2 ዞሯል

## በሶማሊያ የሚሞተው የኢትዮጵያ ሰራዊት ብዛት አስደንጋጭ እየሆነ ነው፣ የሚከዳው ሰራዊት ቁጥርም ጨምሯል፣

ወያኔ መራሹ የኢትዮጵያ ጦር፣ ሶማሊያን ከወረረበት ጊዜ አንስቶ በእየቀኑ የሚሞተው ሰራዊት ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን ከግንባር የሚደርሱን መረጃዎች ያመለክታሉ።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ የእስላማዊ ፍርድቤቶች ህብረት በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ የሚፈጽሙትን ጥቃት እያጠናከሩ በመምጣታቸው የሚሞቱ ወታደሮች ቁጥር አስደንጋጭ እየሆነ መምጣቱን የሚናገሩት ምንጮች፣የአገዛዙ ባለስልጣናትም ከሶማሊያ ጠቅልለው ለመውጣት የሚችሉበትን ጥረት ሁሉ እያደረጉ ቢሆንም ሊሳካላቸው እንዳልቻለ ታውቋል። የረሀቡ መባባስና አገዛዙ በሶማሊያ የሚያደርገው ጦርነት ከአለማቀፍ ድርጅቶችና ጋዜጠኞች ትችት መቀስቀሱን ተከትሎ አገዛዙ ሰራዊቱን ከሶማሊያ ፣ወደገጽ 2 ዞሯል

## የግንቦት 7 የኢኮኖሚና ፋይናንስ ክፍል የገንዘብ ድጋፍ መቀበያ ስርአት መዘርጋቱን አስታወቀ

የግንቦት 7 የፍትህ፣የነጻነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ እያደረገ ያለውን ሁለገብ ትግል በገንዘብ ለመደገፍ ከህብረተሰቡ ሲቀርብ የነበረውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የባንክ አካውንትና በድረ-ገጹ የፔይ-ፓል (Pay-pal) አሰራር መጀመሩን የኢኮኖሚና ፋይናንስ ክፍሉ አስታወቀ።የተዘረጋው አሰራር ከየትኛውም የአለም ክፍል ለሚደረጉ ገንዘብ ነክ ድጋፎችን ለመቀበል እንደሚያስችልና፣አሰራሩም ቀልጣፋና ለጋሽ ወገኖች በሚፈልጉት መንገድ ሊከናወን እንደሚችል የክፍሉ ሃላፊ ለግንቦት 7 ልሳን ገልጸዋል።እንደ ሃላፊው አገላለጽ ከሆነ፣የአሰራር ስልቱ የድጋፍ ሰጭ ወገኖችን የግል መረጃና ሌሎች ጉዳዮች ዝርዝር ሳያስፈልግ ከባንክ ወደ ባንክ በሚደረግ የገንዘብ ዝውውር ብቻ መከናወን እንደሚችል አስረድተዋል።ይህው የክፍያ ስርአት ፔይ-ፓል(pay-pal) በንቅናቄው ድረ-ገጽ www.Ginbot7.org ከትናንት ጀምሮ ወጥቶ ስራ መጀመሩ ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሃገር ቤት የሚገኙ የንቅናቄው ደጋፊዎች ድጋፍ የሚያደርጉበትን አሰራር በተመለከተ የሃገር ውስጡ አካል በቅርቡ የድጋፍ መሰብሰቢያ ስልቱን እንደሚዘረጋ የንቅናቄው የኢኮኖሚና ፋይናንስ ክፍል ተጠሪ ጨምረው ገልጸዋል። ንቅናቄው ለተያያዘው ሃገርንና ህዝብን የማዳን ትግል በተለያዩ ዘርፎች ተግባራዊ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆና፣እነዚህን ለፍጻሜ ለማብቃት ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን አስፈላጊውን የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት የዜግነት ግዴታቸውን እንዲወጡ የንቅናቄው የፋይናንስ ክፍል ተጠሪ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

# ርእሰ አንቀጽ

## ከሀሰተኛ መሪዎች መላቀቂያው ጊዜ አሁን ነው

አንድ ገጣሚ ባንድ መድብሉ እንዲህ ገጥሞ ነበር፦

ወዮላት ለዚያች አገር፣ህዝቦቿ እንደበግ ለሆኑባት
እረኞች ወደገደል ለሚመሯት፣ተኩላዎች ለተሰገሰጉባት
ወዮላት ለዚያች አገር፣ዋሾ መሪዎች ለሞሉባት
ምሁሮቿ ለታፈኑባት፣ጭፍንተኞች ለተንሰራፉባት
ወዮላት ለዚያች አገር፣ ድምጻን ማሰማት ለተሳናት
ወራሪዎች ለሚሞገሱባት፣ደደቦች ጀግና ለሚሆኑባት
ወዮለት ለዚያ ህዝብ፣ ነጻነቱን እንዲቀማ ለፈቀደው
መብቱን አሳልፎ ለሰጠው፣በአገሬ እንባ ገላውን ለታጠበው

አዎ፣ ወዮላት ለዚያች አገር፣ በህልም እንጀራ ለሚኖርባት፣ ህጻናት እንደቅጠል ለሚረግፉባት፣ ወዮላት ለዚያች አገር፣ወጣቶች በጦርነት ለሚማገዱባት፣ መሪዎቿ በቅምጥል ለሚኖሩባት፣ ወዮላት ለዚያች አገር፣ህዝቦቿ በጠኔ ለሚሞቱባት፣ሀሳብ በነጻነት ለማይገለጽባት፣ መሪ በፍላጎት የማይሾምባት፣ ወዮላት ለዚያች አገር፣ፍቅር ለሞተባት ጥላቻ ለነገሰባት...ወዮላት ሊዘያች አገር ወዮላት።

አንድን አገር አገር የሚያደርገው ወይም ከአገር ተርታ አውጥቶ የአገር ጭንጋፍ የሚያደርገው መሪው ነው። ጥሩ መሪ የአገሩን ህዝብ አጥግቦና አስደስቶ ያኖራል፣ በችግር ጊዜ ከህዝቡ ፊት፣በደስታ ጊዜ ከህዝቡ ጀርባ ይሰለፋል። ሙገሳውን ለህዝብ ይሰጣል፣ትችቱን ለራሱ ይወስዳል፤ አገልግሎቱን በጨረሰ ጊዜም ለለተኪው መሪ በፍቅርና በሰላም ሀላፊነቱን ያስረክባል።ታሪክም ይዘክረዋል፣ህዝብም በመሪው እየኮራ ፣አገሩን እየወደደ ይኖራል።ጥሩ መሪ የሌለው ህዝብ ግን ዘለአለም በአገሩ እንደተሸማቀቀ፣ የመሪውን ስም ለመጥራት እንዳፈረ ይኖራል። የጥሩ መሪ መለኪያው ብዙ ነው፤ከሁሉም በላይ ግን ታማኝ ሆኖ መገኘቱ ነው። መሪ ለራሱና ለሚመራው ህዝብ ታማኝ ሆኖ መገኘት አለበት። ለራስና ለህዝብ ታማኝ መሆን አለበት ሲባል ከተራ አታልይነት ባህሪ ተላቆ እውነትን የታጠቀ መሆን አለበት ማለት ነው። ብዙ አታላይ መሪዎች አለምን ወደጥፋት ሲመሯት ከታሪክ ተምረናል።ውሸት የሚያስከፍለው ዋጋ ብዙ ነው።ውሸትን በእውነት ለመተካት፣ከዋሹ በሁዋላ እንደገና ታማኝነትን ለማግኘት እጅግ ከባድ ነው። ይህንንም በመለስ ዜናዊ እያየነው ነው።መለስ ዜናዊ ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ አንድም ቀን ውሸት ሳይናገር መስከረም አልጠባም። ብዙ ጊዜ ውሸታቸው የሚጋለጠው ሳይውል ሳያድር ነው።የሰሞኑ የርሀብ ዜና ጥሩ ማሳያ ይሆነናል።ያለፈው ሚያዚያ ወር፣ የአለማቀፍ ድርጅቶች "በኢትዮጵያ የተራበው ህዝብ ቁጥር ከ10 ሚሊዮኖች ይበልጣል" ብለው ሲናገሩ፣ የወያኔ ገዢዎች ቡራ ከርዩ አሉ። አዲሱ ለገሰ "የእርዳታ ድርጅቶች በኢትዮጵያ የተገኘውን የኢኮኖሚ ድል ያንቋሽሻሉ፤በአገራችን የምግብ እጥረት ያጋጠመውን ህዝብ ቁጥር እያጋነኑ በማቅረብ ድርጅቶቹ፣ የእርዳታ መለመኛ አደረጉን" ብሎ መግለጫ ሰጠ። አሁን ጊዜው ደረሰና ጉዱ ፈላ። እነ ስምኦን መቻሌ ከሳምንት በፊት የተራበው ህዝብ ቁጥር ከተገመተው በላይ ነው ብለው ተማጽኖ አቀረቡ፣እንዲያውም የእርዳታ ድርጅቶች በቂ ስራ አልሰሩም ብለው ወቀሱ።ተመልከቱ ትናንት በስማችን እርዳታ ሊጠይቁብን ነው ብለው አፈርድሜ ያበሏቸውን ድርጅቶች ዛሬ ስራ አልሰሩም ብለው እንደገና መውቀስ ያዙ። መደናበራቸውን የሚያሳው ደግሞ እነስሞን መቻሌ የተናገሩት ሳይደርቅ፣ መለስ ዜናው በታይም መጽሄት ላይ ዩኒሴፍ ያስቀመጠውን ቁጥር በመተቸት መግለጫ ሰጠ።"...በኢትዮጵያ ረሀብ የለም።በየጊዜው የሚከሰቱ ችግሮች አሉ። ይህን አለመገንዘብም ደደብነት ነው። የአስቸኳይ የምግብ እርዳታዎች ያስፈልጋሉ።ረሀብ ግን የለም።" አለ መለስ። በርግጥም የአለማቀፍ ድርጅቶችና ጋዜጠኞች ባያጋልጧቸው በውሸት ህዝባችንን በረሀብ ያስፈጁት ነበር።

እንዲህ አይነት ፈጣጣ ውሸታም መሪዎች ናቸው ነው እንግዲህ ለ17 አመታት የገዙን። በውሸት ሲቀልቡን፣ በውሸት ሲያጠጡን፣በውሸት ሲያለብሱን እስከዛሬ የተገዛንላቸው ለእነዚህ ውሸታም መሪዎች ነው። አሁን ግን በውሸት መኖርን በቃን ብለናል። በውሸት መኖርን የምትጠሉ፣ ለእውነት የምትቆሙ ሁሉ ተነሱ።የእውነት ሀይሎች በእየበሮቻችሁ ቆመዋልና።ዛሬውኑ ግንቦት7 ንቅናቄን በመቀላቀል ኢትዮጵያን ከውሸተኞች፣ህዝባቸውን በውሸት ከሚገድሉ ጨቋኝ መሪዎች አላቋት።ከውሸተኛ፣ከገዳይና አምባገነን መሪዎች መላቀቂያው ጊዜም አሁን ነው።

## "ረሀቡ እየከፋ ስለሆነ ..." ከገጽ 1 የዞረ

የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትሩ አቶ አዲሱ ለገሰ "ረሀብ ተከስቷል እያሉ ችግሩን እያጋነኑ ያሉት አንዳንድ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ናቸው፤ችግሩ ከቁጥጥራችን እንደማይወጣ አረጋግጥላችሁዋለሁ " ብለው ፓርላማው ፊት በተናገሩ ሁለት ወራት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ፤ ምክትላቸው ዶክተር አበራ የድረሱልን ጥሪ ማቅረባቸው ብዙዎችን ፈገግ ከማሰኘቱም በላይ፤ "የአሁኑን የተማፅኖ መግለጫ አቶ አዲሱ ያልሰጡት ስለማያምርባቸው ነው" አሰኝቷል።

## በሶማሊያ የሚሞተው የኢትዮጵያ ከገጽ 1 የዞረ

ለማስወጣት የሼሪያ ፍርድቤቶች ባለስልጣናትን ለማነጋገርና ለማሳመን ደፋ ቀና እያለ እንደሚገን ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል።በዚህ ሁኔታ የተበረታቱት የሶማሊያ ታጣቂዎች ልመናውን ወደጎን በመተው ተደጋጋሚ ጥቃት በመሰንዘር ላይ ሲሆኑ፣ በዚህም ምክንያት በርካታ የኢትዮጵያ ወታደሮች እየሞቱ እንዳለ ለማወቅ ችለናል።እንዳገኘነው መረጃ ከሆነ በእስካሁኑ ጦርነት በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት አባላት የሞቱ ሲሆን፣ የሟች ወታደሮችን ቤተሰቦች ላለማርዳት ወያኔ መረጃውን አፍኖ መያዙን ለማወቅ ተችሏል።ለዚህም የሚሰጠው መልስ ከኤርትራ ጋር በሚደረገው ጦርነት ላይ ተጽኖ ያመጣል የሚል ነው።እንደ መረጃዎች ከሆነ ፣ ወረራው ሲፈጸም ከሞቱት ወታደሮች ይበልጥ በቅርቡ በደፈጣ ውጊያውና በጎዳና ላይ በተጠመዱ ፈንጂዎች የሞቱት የሰራዊት አባላት ቁጥር ይበልጣል። የጦር መኮንኖቹ እንደሚናገሩት አብዛኞወቹ ወታደሮች የሚሞቱት የኢትዮጵያ ጦር አጋር መስለው በሚቀርቡ፣ የእስላማዊ ፍርድቤቶች ደጋፊ በሆኑ ሽማቂዎች ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በማይረባ ጦርነት ወንድሞቻችን በበረሀ እንዲረግፉ እየተደረገ ነው፣ጦርነቱ ይቁምልን ብለው ጥያቄ ማቅረባቸው እየተሰማ ሲሆን፣ በተለይ ጥያቄውን ያቀረቡት የሰራዊቱ አበላት ጥቃት እየደረሰባቸው መሆኑን ምንጮቻችን ዘግበዋል። ጦርነቱን በመቃወም ወያኔን የሚከዱና ተቃዋሚ ቡድኖችን የሚቀላቀሉ ወታደሮች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፣ እነዚህን ወታደሮች የማደራጀት ስራ በተቃዋሚዎች በኩል እየተሰራ መሆኑም ታውቋል።

### ግንቦት 7 የፍትህ፣የነጻነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

**ጀግኖች አትሌቶቻችን በቤጂንግ ኦሎምፒክ አንጸባራቂ ድል እንዲቀዳጁ በኢትዮጵያ ህዝብ ስም ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል።**

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## ሃገርን ከሚበድል፣ወገንን ከሚገድል፣ ከሃዲ ጋር ማበር የከፋ ወንጀል ነው፤

### ለሃገር መከላከያ፣የደህንነት፣ የፖሊስ ሰራዊት አባላትና አመራሮች በያላችሁበት፣

ይህን ከወገን ጋር አብሩ፣ለዴሞክራሲ ስርአት ስሩ፣አምባገነንነትን ለማጥፋት ተባበሩ፣ የሚል የታሪክ የህሊናና የወገን ጥሪ የምናደርገው፣ዛሬ ከመቸውም ግዜ በላይ ህዝብ በድህነት አዘቅት ተደፍቆ፣በአምባገነንነት ስር ማቆ፣የሃገር ሃብት ተሰርቆ፣ሉአላዊነት ተፍቆ በሚገኝበት አስቸጋሪ ወቅት በመገኘታችን ነው።የዚህ ሁላ መከራና አበሳ፣እንዲሁም ትርምስ መንስኤ እየሆነና በመሆን ላይ ያለው የመለስ መንግስት በህዝብ ተተፍቶ፣በስብሶና ተበላሽቶ፣የሚደግፈው አጥቶ ብቸኛ መንጠላጠያው እናንተ ከህዝብ አብራክ የወጣችሁ፣በድሃው ገበሬ ገንዘብ የተማራችሁ፣ወገን በሚሰጠው ታክስ የተሰማራችሁ ሰራዊት አባላት ላይ እንደሆነ እናንተም እኛም የምናውቀው ሃቅ ነው።ለመለስና አገዛዙ የስልጣን እድሜ መራዘምና የጥንካሬ ምንጭ እናንተ የሰራዊት አባላት እንጂ ቅንጣት የህዝብ ፈቃድ እንዳልሆነም የምታጡት አይመስለንም።የአገዛዝ ስርአቱ በገዛ ወገናችን ወገናችሁ ላይ የሚፈጽመው በደል እናንተ ባነገባችሁት መሳሪያ፣ባላችሁ የሙያ እውቀትና ችሎታ፣ቀን ከሌት በምትሰጡት አገልግሎት፣በምትከፍሉት የአካልና ህይወት መስዋእትነት እንጂ በሌላ ሰማያዊም ሆነ ምድራዊ ሃይል ረዳትነት ከቶም አይደል።የእናንተን አቅም በመጠቀም በገዛ ወገናችሁ ላይ ግድያ ይፈጽማል፣በእናንተ ከለላነት የሃገር ንብረት ወደውጭ ያሸሻል፣በምትከፍሉት የደምና ሕይወት ዋጋ የሰው ሃገር ይወራል።በዚህም ከገዛ ወገናችሁ ጋር ደም እንድትቃቡ ፣ህዝቡም በጥርጣሬና በጥላቻ አይን እንዲመለከታችሁ እያደረገ ነው።

ውድ የሰራዊት አባላት፣ የመለስን አገዛዝ እድሜ ለማራዘም ሲባል ብቻ በአሁኑ ወቅት በሱማሊያ በረሃዎች መንገላታትህ ሳያንስ፣በሞቃዲሹ ጎዳናዎች የሚጎተተው የከበረ ሙት ኢትዮጵያዊ ወታደርን አስከሬን በየቴሌቪዥን መስኮት አይተን ሰቅቆናል።ይህ ሆኖ እያለ በምእራብ አቅጣጫ በሱዳን ድንበር በኩል ሃላፊነት በጎደለው ስሜት፣የሃገራችንን ሉአላዊ መሬት የመስጠቱን ክህደት ይብቃ ካላልን፣ በዛሬ እኛነት ብቻ ሳይሆን በነገ ትውልዶቻችንን ህልውናና ክብር ላይ ለሚደርስው አደጋ እንደመተባበር ይቆጠራል።

የጥሪያችን መነሻ አሁንም ለእናንተ ካለን የወገን ተቆርቋሪነት እንጂ ከናንተ የምንሻው ሌላ ነገር ኖሮን አይደለም።ደግሞም ግዜ ሳይረፍድ ለማንም ሳይሆን ለዛሬ ራሳችሁና ለነገ ልጆቻችሁ ስትሉ ዛሬን በመኖር ነገን ከመግደል በመቆጠብ፣የህዝብ አሌንታነታችሁን እንድታረጋግጡ ነው።ለጥቂት አምባገነን መሪዎች ሲባል የምትከፍሉት መስዋእትነት ከንቱ፣ የምታፈሱት ደም ደመ - ከልብ፣የምትገብሩትን የህይወት ዋጋ መና የሚያስቀር ተግባር ውስጥ እንዳላችሁ ማወቅ አለባችሁ።ከመለስ ዜናዊ የግል ሰራዊትነት እራሳችሁን ወደ ህዝባዊና ሃገራዊ ሰራዊትነት የምትለውጡበትም ጊዜ ቀርቧል።

ይህን ጥሪ ስናቀርብ እናንተም በምን አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳላችሁ በቂ የሆነ እውቀቱ አለን።ካለፉት የ17 አመታት ልምድ እንደምትረዱት መለስና አገዛዙ እንኳን ለእናንተ ለራሱ ሰዎችም የማይመለስ የሰብአዊነት እንጥፍጣፊ የጎደለው አራዊት መሆኑን ነው።በደሞዝና ጥቅማጥቅም፣የዝውውርና የማእረግ እድገት፣በትምህትርት እድልና ራስን ለማሻሻል በሚመጡ እድሎች በራዊቱ መሃከል ምን ያህል በመድሎ እንደሚሰራ ስለምናውቅ ከማንም በላይ ይሰማናል፣ህሊናችንም ይደማል።በራሱ የማይተማመነው ይህ ስርአት በየጊዜው በሰራዊቱ አባላት መሃከል መተማመን እንዳይፈጠር በዘረጋው የግም-ገማ አሰራር ስርአት ምን ያህል እንደምትሳቀቁ ይገባናል።አንዱን ታማኝ አብዛኛውን የማይታመን፣ለአንዱ ተደራራቢ ሃላፊነትና ሹመት የተቀራችሁት ከአንዱም ተከልክላችሁ፣ እድገትና ማዕረግ በስራ ትጋትና ችሎታ ሳይሆን መለኪያው ሌላ እንደሆነ ስናስብ የእናንተ ብቻ ሳይሆን የእኛም ቆሽት ይበግናል።

በዚህ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ እያላችሁ አደጋ በተፈጠረ ቁጥር እናንተን የግንባር ስጋ በማድረግ በህዝብና በሃገር እያስጠሉ የተንደላቀቀ ኑሮአቸውን በቤተመንግስታቸው ሲቀጩ፣ የእናንተና የቤተሰቦቻችሁ ኑሮ ግን አስከፊ በሆነ አዘቅት ውስጥ እንደሚገኝም ይታወቃል።

እንደ ከዚህ ቀደምቶቹ ስርአቶች መለስና አገዛዙ ዘላለማዊ አይደሉም፣መውደቃቸው የጊዜ ጉዳይ እንጂ የማይቀር እውነታ ነው። አሁንማ እየተፈጠረ ያለው ቀውስና የህዝብ ልጆች በሚያደርጉት ተጋድሎ የስልጣን ዘመናቸው ሊገባደድ ቀናት እንደሚቆጠሩ አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።ከዚህ ካለቀለትና እየሞተ ካለ ስርአት ጋር በመወገን በህዝብ ላይ በሚፈጸም በደልና ግፍ ተባባሪ በመሆን ነገ ከነገ ወዲያ በታሪክና በህዝብ ፊት እንደሚያስጠይቃችሁ፣እንደሚያስገምታችሁም አውቃችሁ እርምጃ ውሰዱ።ከእንግዲህ ወዲያ የእናንተ አፈሙዝ በህዝብ ወገኖች ላይ ሳይሆን የአገዛዙ መሪዎች ላይ ማነጣጠር አለበት፣የእናንተ ጥይት በአገዛዙቀ ቀንደኛ አጋፋሪዎች ላይ መተኮስ አለበት።

ከህዝብና የዴሞክራሲ ሃይላት ጋር በመወገን የአምባገነናዊውን አገዛዝ ግብአተ መሬት በጋራ ፈጽማችሁ፣ ነገ በምትገነባው ነጻይቱ ኢትዮጵያ የስራ፣የደሞዝ፣የእድገትና የማእረግ ዋስትናው የተጠበቀ የህዝብ ወገን፣ በህዝብ የተወደደ የሰራዊት አካል ለመሆን አስፈላጊውን የአእምሮ ዝግጅት በማድረግ ለወሳኙ ፍልሚያ ግንባር ቀደም ሁኑ እንላለን።

ውድ የሰራዊት አባላት፣ወገናችሁና ሃገራችሁ ከናንተ ዛሬ የሚጠብቁት ነገር፣በዛሬው እለት ጊዜ ወስዳችሁ ከገዛ ህሊናችሁ ጋር ተማክራችሁ ለዚህ ትግል የአቅሜን እወጣለሁ የሚል የግልና የቡድን ውሳኔ ላይ መድረስ ነው።ከመድሎ የነጻች ለሁላችንም የምትሆን ሃገርን ለማየት የምንፈልግ ወገኖች ሁሉ፣በየመስኩ አስፈላጊውን የትግል አስተዋጽኦ በማድረግ በህገ-መንግስትና በህዝብ ፈቃድ የሚመራ ስርአት የማቆም ራዕያችንን እውን ማድረግ እንችላለን።

ለትግሉም ስኬታማነት እራሳችሁን በማዘጋጀት በተገቢው ጊዜና፣ ጥሪ በሚደረግበት ወቅት አለማወላወል ህዝባዊነታችሁን አስመስክሩ እንላለን።አሁንም ቢሆን አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የአገዛዝ ስርአቱን በመወገን በሚጣልላቸው ፍርፋሪ በመታለል በህዝብ ወጎኖች ላይ በሚፈጸም ወንጀል ተባባሪ የሆኑ፣ከቀድሞ መንግስት ሰራዊት መበተን እና ሌሎች ታሪካዊ ሁኔታዎች ያልተማሩ፣ ይህ መውደቁ የተረጋገጠ ስርአት እንደማያስጥላቸውና የነግ እድላቸውን እያበላሹ እንደሆነ እንነግራቸዋለን።

ለውድ ወገን ለሆናችሁ የሰራዊት አባላት ከፊታችሁ ሁለት ምርጫ ያለ ይመስለናል፣ከህዝብ ጋር መወገን ወይም አለመወገን፣ዛሬን እየበሉ መኖር ወይንም ነገን አለመኖር።የአምባገነንነት ስርአትና የመለስ ዜናዊ የግል ሰራዊት ሆኖ ሕይወትን ለከንቱ ምክንያት ከማጣት፣የህዝብ ወገንተኝነትን አስመስክሮ ከማያልፍ ታሪክ ጋር ማለፍን የመሰለ ምርጫም የለም።ህሊና እንዳለው ሰብአዊ ፍጡር ምርጫውን ለእናንተ ብንተውም፣እንደወገንነታችን ዛሬን ለመኖር ነገን ከመግደል በመቆጠብ ዘላቂ ጥቅም ያለው ምርጫ እንድትመርጡ እንመክራቹሃለን።

**ከወገን-ለወገን የተደረገ ጥሪ**

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## ውጡ! የነፃነቱን ጉዞ ተቀላቀሉ!

ጋቹዬ

ታሪኳን ዘ-ቨርጂየር የተሰኘች መፅሐፍ ውስጥ ነው ያገኘሁዋት፦ ሰውየው ፈፅሞ ማንበብና መፃፍ አይችልም ።አልተማረም ብቻ ሳይሆን ከተፈጠረ ጀምሮ በትምህርት ቤት ደጃፍ አልፎ አያውቅም። እንግሊዝ አገር በምትገኝ የአንዲት የቅድስት ማርያም ገዳም ውስጥ በዕቃ ግምጃ ቤት ጠባቂነት ለረዥም ዓመታት ሲያገለግል ቆዬ።የሚውለውም የሚያድረውም እዚያው ስለሆነ የውጭውን ዓለም አያውቀውም።ሆኖም፤ ከዕለታት አንድ ቀን የገዳሙ አስተዳደር አዲስ መመሪያ አወጣ-“በገዳሙ ውስጥ የሚሰሩ በሙሉ ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው” የሚል።እናም አበምኔቱ ወደ ዕቃ ግምጃ ቤቱ ጠባቂ በመምጣት **“አዲሱ መመሪያችን እንደ አንተ ዓይነቱን ያልተማረ ሰው በስራ ለማስቀጠል ስላልፈቀደልን ካሁን ሳት ጀምሮ ከስራ ተሰናብተሃል”አሉት።**

ጆሮን ጭው የሚያደርግ መርዶ የሰማ ያህል ለጊዜው በድንጋጤ ክው ብሎ ቀረ።ፍርሀት እጅና እግሩን አሰረው። ሆኖም ምንም ማድረግ ስለማይችል ውሳኔውን በፀጋ እንደሚቀበለው ለአበምኔቱ ነገራቸው።እናም የአገልግሎት ክፍያውን በመቀበል ለዘመናት የቆየባትን ገዳም ለቆ ወጣ::

ልክ ከገዳሙ ወጥቶ ጉዞ እንደጀመረ በህልሙም በውኑም ትዝ ብሎት የማያውቀው ሲጃራ አሰኘው።ሆኖም፤ በገዳሙ ዙሪያ በተንጣለለው አገር የሚያህል ሜዳ፤ አልፎ አልፎ ከሚሰማ የወፎች ጫጫታ ውጭ አንዳችም ዝር የሚል ነገር አይታይም። ስለዚህ ረዥሙን ሜዳ እያቆራረጠና እግረ-መንገዱን የሲጃራ መሸጫ ሱቅ እየፈለገ ጉዞውን ቀጠለ።

ከረዥም ጊዜ በሁዋላ አንዲት ከተማ ላይ ቢደርስም አሁንም ያሰኘውን ሲጃራ በከተማዋ ሊያገኝ አልቻለም።ልክ እንደ እርሱ በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች በሲጃራ እጦት ሲብሰከሰኩ ተመለከተ።እዛ መቆየቱ ምንም ዋጋ እንደሌለው ስለተገነዘበ ወደፊት ጉዞውን ቀጠለ።ከጥቂት ጉዞ በሁዋላ አንዲት ሌላ ከተማ ላይ ደረሰ-የሲጃራ መደብሮችና ሱቆች እንደ አሸን የፈሉባት ከተማ ማለት ነው።ገዛ፣ለኮሰ፣ አጨሰ።

እያጨሰም አንድ ሀሳብ ወደ ልቡ መጣለት፦”ለምን ከእዚህ ሲጃራ እየወሰድኩ- እዚያ ሲጃራ የሌለበት ከተማ አልሸጥም?” የሚል።አደረገውም።

ዘሀር ቆመለት።በችርቻሮ ጀምሮ በጥቂት ወራት ውስጥ የበርካታ ሲጃራ መደብሮች ባለቤት እስኪሆን ድረስ እጅግ ትርፋማ ሆነ።ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ከመደብር ባለቤትነት ወደ ሲጃራ ኩባንያ ባለቤትነት አደገ።በዚያው ዓመት በእንግሊዝ አገር በታየው፤ የግል ኩባንያወች የንግድ እንቅስቃሴ ውድድር፤ከመላ አገሪቱ አንደኛ ትርፋማ ባለሀብት ሆኖ ተመረጠ።በእንግሊዝ የሚገኝን አንድ ታላቅ ኮመርሻል ባንክ በአክስዮን ለመግዛት ጨረታውን ካሸነፉ ጥቂት ባለሀብቶች፤ አዲሱ ሚሊየነር አንዱ ነው።እናም እጅግ በርካታ ህዝብ ወደተሰበሰበበትና የአክሲዮን ሽያጩ ወደሚካሄድበት ስፍራ በሊሞዚኑ አመራ።የኩባንያው ዝና እጅግ ስለናኘ አዲሱን ሚሊየነር ለማየት እጅግ በርካታ ሰዎች ታድመወል። በቦታው ደረሰ። የባንኩ ሥራ አስኪያጁ በኦፊሴል ደረጃ ካስተዋወቁትና የእንኳን ደስ ያለህ ንግግር ካደረጉለት በሁዋላ፤ በአክስዮኑ ቅፅ ላይ ሰሙን በመፃፍ ፊርማውን እንዲያኖር ጠየቁት፣**“ስሜን መፃፍ አልችልም”**ሚሊየነሩ መለሰ።ሁሉም ይበልጥ መገረም ሞላባቸው።**”እሽ ፊርማህን ታኖርልን?”**ሥራ አስኪያጁ በድጋሚ ጠየቁ፣ታዳሚው ይበልጥ ጆሮውን ቀስሯል፣**“መፈረምም አልችልም”**-ቆፍጠን ብሎ መለሰ።በሁኔታው እጅግ ግራ የተጋቡት የባንኩ ሥራ አስኪያጅም አሉት፦**”ማንበብና መፃፍ ሳትችል ለዚህ ከበቃህ ብትማርማ ኖሮ የት ትደርስ ነበር?”“… ብማርማ ኖሮ…”**አለ አዲሱ ሚሊኒየር በምፀት ወደ ሁዋላ ሂዶ እያውጠነጠነ

**“ብማርማ ኖሮ..የቅድስት ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ዕቃ ግምጃ ቤት ጠባቂ ሆኜ እቀር ነበር”**

ይህን ታሪክ የጠቀስኩት “በፔዳጎጅ ሰነፍ አስተማሪ እንጅ ሰነፍ ተማሪ የለም” በሚል ስለ ትምህርት አሰጣጥና አቀባበል ወይም ስለሰው ልጆች ድብቅ ክህሎት(ታለንት) ለመናገር አይደለም-ውጡ!አትፍሩ! የነፃነቱን ትግል ተቀላቀሉ ልላችሁ እንጂ።ገጣሚው፦ “ተኖረና ተሞተ “ እንዳለው የአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮ ከዕቃ ግምጃ ቤት ጠባቂነት የተሻለ አይደለም።ከድህነት ወለል በታች ሌላ ወለል እየተፈለገልን ባለበት ባሁኑ ወቅት፤ገዥዎቻችን ስለኢኮኖሚያችን ማደግ ይነግሩናል።በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የግፍ አገዛዝ፣የመብት ረገጣ፣አድሏዊነት፣ጭቆና፣ ባርነት፣ድህነት፣ረሀብ ይበልጥ ተንሰራፍቷል።አገሩን ከውጪ ወራሪዎች በመከላከል በተደጋጋሚ ታሪክ መስራቱ የሚመሰከርለት የኢትዮጵያ ህዝብ፤ በየጊዜው ከገዛ አብራኩ በሚወጡት ገዥዎች ከመረገጥ ፋታ ሊያገኝ አልቻለም። እኩልነት፣ፍትህ፣ዲሞክራሲ፣ ነፃነትና ብልፅግና ቀበቶ አጥብቆ የመታገልን ዋጋ ጠይቀውናል።ለዚህም ነው ግንቦት 7 ፤ማቆሚያ በሌለው የአገዛዙ ችግር “ካሉት በታች ከሞቱት በላይ” የሆነው አብዛኛው ህዝባችን፤ የእቃ ግምጃ ቤት ጥበቃ ዓይነት የሆነውን ኑሮ ለቆ መውጣት አለበት የሚለው።

***ውጡ!የነፃነቱን ትግል ተቀላቀሉ!***

ብዙዎቻችን ከተለመደው የኑሮ አዙሪት ሰብሮ ለመውጣት ስለምንባባ ትርጉሙ በጠፋበት ህይወት ለዘመናት የማያባራ ዋጋ ለመክፈል ተገደናል።ግን..እስከመቼ በዚህ እንቀጥል? ደግሞ ከዚህስ በላይ ምን ሊደርስብን ነው መርግ የሚያህል ግፍ ተሸክመን ዝም ያልነው?ነፃነት በተገሰሰበት፣መብት በተረገጠበት፣ጠመንጃ በገነነበትና ረሀብ ትርፍ በሆነበት አገዛዝ የመኖር ትርጉሙ ምንድነው?ይህን የጭቆና ቅጥር ሰብሮ ለመውጣት የሚያስፈራውስ ምንድነው?መኪናዋ በጭቃ ተይዛ ስትንደፋደፍ “አንድ፣ሁለት፣ሦስት፣” የሚል አስቆጣሪ የምንጠብቀው እስከመቼ ነው?ዛሬውኑ እያንዳንዳችን እንነሳ! አፋኙን ቅጥር ሰብረን በመውጣት የተሻለውን ጉዞ እንጀምር።ሌላው ቢቀር ለልጆቻችን በአጭር ጊዜ የሚደርሰውን ቴምር አሁኑኑ እንትከል።

***ውጡ! የነፃነት ትግሉን ተቀላቀሉ!***

አቶ መለስ ዜናዊ በሥልጣን ማግስት “አሰር” ከተሰኘ የኤርትራ መፅሔት ጋር ባደረገው ቃለ-ምልልስ ፤እንዴት ወደ ትግል ህይወት እንደገባ ለቀረበለት ጥያቄ በሰጠው መልስ ፤የመንግስቱ ሀይለማርያም አገዛዝ ጭቆናውን እያከፋው መምጣቱ ለትግል እንዳነሣሳሳው ከገለጸ በሁዋላ፦”በባርነት ከምኖር ሞቴን እመርጣለሁ”ነበር ያለው።ታዲያ ዛሬ የእርሱ አገዛዝ ከመንግስቱ በከፋ መልኩ ቀንበሩን ሲጭንብን እኛ ምንድነው ማለት ያለብን?ዛሬ አቶ መለስ፦”መንግስቱ በአለንጋ ገርፏችሁዋል፤እኔ ደግሞ በጊንጥ እገርፋችሁዋለሁ”ሲለን፤ ምንድነው ማድረግ ያለብን?በባርነት መኖር? ወይስ “በባርነት ከምኖር ሞቴን እመርጣለሁ!”ብሎ ለነፃነት መታገል?አዎ! የቆየ የህይወት ልምድና ባህል ነውና ፤ ከዕቃ ግምጃ ቤቱ ክልል ለመውጣት ስንወስን “ጓደኛ፣ዘመድ፣ቤተ-ሰብ ፣መንደር፣ቀየ….”የሚል ዝብርቅርቅ ስሜት መፈጠሩ አይቀርም።በዚያ ላይ በባህርይው የትግል ጉዞ ከባድነት ይታወሳል። ይህም ስሜት፤ ፍርሀትን በመፍጠር በኩል የራሱ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል።ጀግንነት ማለትም ፍርሀት አለመኖርን አያመለክትም_በነዚህ ስጋቶችና ፍርሀቶች ላይ መድፈርን እንጂ።ስለዚህም ሁላችንም በፍርሀቶቻችን ላይ ደፋር ውሳኔ እናሳልፍ! ለዘመናት ያሰረንን የዕቃ ግምጃ ቤቱን ክልል ለቀን በመውጣት በነፃነቱ የትግል ሜዳ እንጓዝ!የብልፅግናና የድል ፍሬ የሚታጨደው እዛ ላይ ነውና።